# <u>እግዚአብሄር ታላቅ ነገርን አደረገልን ደስም አለን</u> <u>መዝ 125:3</u>

## <u>*ያህዌህ ይርኤ እግዚአብሔር ያያል*</u>

**(ከተክለ ማርያም ሳዉዝ አፍሪካ ጆሃንስበረግ)**

በቤተክርስቲያናችን አውደምህረት ከጥር ሥላሴ ዋዜማ ጀምሮ ዘወትር በታላቁ መምህር የክርስቶስ ወንጌል ሀዋርያ በተወደጁ አባታችን በአባ ወልዴ የህይወት ብፌ ተዘርግቶልን ሰነባብቷል።



ጥር 20 ቀን 2002 የእመቤታችን ዋዜማ በአይነቱ ለየት ያለ የደስታ ቀናችን ነበር የጆሀንስበርግ ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ህንፃዋን በሀገራችን ባንዲራ ዙሪያዋን ጠምጥማ በማሸብረቅ እና ከሩቅ በጥኡም ሽታው እያወደ የሚጠራውን የዕጣን ሽታ እያስማገች ለበአሉ ድምቀት ሰጥታለች በአካባቢው የሚገኘው ምዕመናን በሙሉ ሰምቶ የቀረ የለም ከወትሮው በተለየ ትልቅና ግዙፉ ካቴድራል ቤተክርስቲያናችን ጢም ብሎ ሞልቷል። በኋላ የመጡት ምዕመናን በውጭው የክርስትና ማጥመቂያ ክፍል ሳይቀር ተቀምጠዋል የዘገዩትም በበሩና በውጭ ሆነው በመቆም በመርሀ ግብሩ መሰረት የሚሰጠውን አገልግሎት በድምፅ ማጉያ ሲከታተሉ ተስተውሏል አቤት በስደት አንድነታችን ሲያስደስት እንዲህ እኮ ነን ድሮውንም የተዋህዶ ልጆች!!

ከአበውም እንደተረዳነውና በታሪክም እንዳየነው በሀላችንና ስርዐታችን ጠብቀን በማክበርና እንግዳ የመቀበል ልምድና ፀጋችን እኮ አሁን ድረስ በአህዛብና በሙስሊም እንኳን ሳይቀር ይመሰከርልናል ይነገርልናል።

ይህ ሰሞን ከሌሎች ሁሉ ግዜ ፕሮግራማችን ለየት ብሏል ዘወትር ማታ የወንጌል አገልግሎት ይሰጣል እንግዶች ይመጣሉ ከወራት ቀደም ብለን በጉጉትና በናፍቆት የምንጠብቃቸው ብፁአን አባቶቻችን የቃልኪዳኑን ታቦታት ይዘውልን ይገባሉ ተብሏል እኛም ቀጠሮ ነሽ ፕሮግራም ስራ ነሽ እረፍት ሳይገድበን በስደት እኛን



ወገኖቻቸውን ብለው አባቶቻችን በየአቅጣጫው ተሰብስበው እንዲያውም እኮ ለምንፈልገው ለአገልግሎታችን ትልቅ ስጦታ ይዘውልናል ይኸውም ጌታ ለዮሀንስ በእግረ መስቀሉ የሰጠውን ድንቅ ስጦታ የእመቤታችን መታሰቢያ ከቅዱሳኑ ጋር ይዘውልናል በመፅሐፍ ***እንግዶችን ለመቀበል ትጉ እንግዶችን መቀበል አትርሱ እብራውያን 13:2*** እንዳለ ቅዱስ መፅሐፍ ለዚች ቃል ተገዛን ማለት ነው ለራሳችን በረከት ስንል::

ቁምነገሩ እንዲህ ነው ጥር 20 ቀን 2002 የደስታ ቀናችን ሆነ በጉጉት ስንጠብቅ የነበረውን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን አስተርዕዩ የእረፍት ቀን በአሏን ለማክበር ብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ በካናዳ የኦትዋ ጳጳስ እንዲሁም የአውሮፓና የአፍሪካ ምክትል ጳጳስ እና ዶክተር ናትናኤል በአቡነ ዜና ማርቆስ የህግ ክፍል ሐላፊ ሲጎበኙን ደማቅ አቀባበል በደብሩ መነኮሳትና ካህናት የሰንበት ት/ቤት መዘምራንና ምእመናን ጆሀንስበርግ ኤርፖርት ድረስ በመሄድ በመዝሙር ለዚህ ያደረሰንን እግዚአብሄርን በማመስገን የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሄር ይባረክ እያለ በእልልታ ጥር 19 ከሌሊቱ 6:00 የተቀበላቸው::





የሚገርመው አባ ወልዴ ከእንግድነት ወጥተው አስተባባሪ ሆነዋል መቼም ለእሳቸው የእግዚአብሔር ቤት ሁሉ ቤታቸው ነው እኛም ቤተሰቦቻቸው (የመንፈስ ልጆቻቸው)፡፡

ጥር 20 ቀን ከምሽቱ 12:00 ጀምሮ ለብፁዕ አቡነ መቃርዮስ እሳቸውን ተከትሎ ሊያገለግለንና ሊረዳን ለመጣው ወንድማችን ዶክተር ናትናኤል ልዩ የአቀባበል መርሀግብር ተዘጋጅቷል ምእመኑ በነቂስ ወደ ቤተ - ክርስቲያን ተሰብስቧል በካቴድራሉ ህንፃ የሀገራችን ባንዲራ የማንነታችንና የዜግነታችን ምልክት ሰንደቅ አላማችን ዙሪያውን ተጠምጥሞ ለበአሉ ድምቀት ሰጥቶታል ቀኑም ደግሞ የእመቤታችን ንግስ ዋዜማ ነው እንዲውም እኮ ለእመቤታችንና ለሐገራችን ካለን ፍቅር የተነሳ ባንዲራችን መቀነቷ እንለዋለን አይደል?

ገና ከርቀት የቤተ መቅደሱ የእጣን ሽታ መአዛው እያወደ ይጠራል፡፡



እንግዶችን ለመቀበል በተለያየ መርሀ ግብር የተዘጋጀው መንፈሳዊ ጉባኤ በብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ በፀሎት ተከፍቶ ተጀመረ ከላይ በመግቢያዬ እንደገለፅኩት ሰሞኑን ቀደም ብለው መጥተው አቀባበል ያደረግንላቸው በፍቅር የምንወዳቸው አባታችን መምህር አባ ወልደ ትንሳኤ እኛን በተለያየ ጊዜ እውነተኛ የሆነ ኢትዮጵያዊነት የወገን ፍቅር እርቧቸው በጊዜያዊነት ባእት አድርገው ከሚኖሩባት ከሀገረ አሜሪካ በደስታችንም በሀዘናችንም በባህላችንም በችግራችንም ጊዜ የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ጊዜ ባዘጋጀነው የምዕት አመት ልዩ ፕሮግራም ፈላጊ ያላጣውን ሕዝብ ትተው ለኛ ተገኝተው ከወገኖቻቸው ጋር

በመዋል:: በቅርቡም በዜጎች በተነሳብን የዜኖፎብያ በችግራችን ቀን ሩጠው በቦታው ተገኝተው እራሳቸውን ለመከራም ቢሆን ሰጥተውልናል ኢትዮጵያዊነት የወገን ፍቅርና የክርስቶስን ሀላፊነት ባግባቡ የሚወጡት:: *አለሙም ምኞቱም ያልፋሉ የእግዝአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም የኖራል 1ኛ የሐ 2 :17*




እንደተባለ በአባ ወልደ ትንሳኤ የማያልቀው የዘላለም ህይወት ቃል በሰፊው ተሰበከ በነገራችን ላይ አባ ወልደ ትንሳኤ ከዚህ በተመላለሱበት የአገልግሎት ጊዜ ሁሉም ወንጌላቸውን በሚያስደስት ሁኔታ የሚከታተል ሲሆን ወደ 7 የሚደርሱ ወገኖቻችን ከፕሮቴስታንት ወደ እናት ቤተክርስቲያናቸው መልሰዋቸዋል አያስደስትም የኒህ አባት ስጦታ!



ጉባኤው በመዝሙርና በተለያየ መርሀ-ግብር ቆይቶ ለቃል ኪዳኑ ታቦታት ክብርና ለእንግዶቻችን የእንኳን ደህና መጣችሁ የደስታ ጧፍ አብርተናል መቸም እንግዶችን ከተቀበልንበት ከእመቤታችን ዋዜማ ጀምሮ እስከ እመቤታችንና የመላኩ የቅዱስ ኡራኤል የንግስ በአላችን አከባበራችን ድረስ በሰው ሀገር በአንድ ላይ በፍቅር ተሰባስበን ላየን ሁሉ ሀይማኖታችንና እግዚአብሄርን አስከብረናል፡፡ *ሊቀ ሐዋሪያት ቅዱስ ጴጥሮስ በመጀመሪያ መልእክቱ ምዕራፍ 2:13 እግዚአብሄርን ያከብሩት ዘንድ በአህዛብ መንከል ኑሮአችሁ መልካም ይሁን* እንዳለ እኛም ሁለንተናችን በአህዛብም እንኳን ሁሉ መልካም ሆነልን፡፡ እድሜ ለአበው ስርአተ ቤተ - ክርስቲያን ተጥሶ በግፍ ለተሰደዱት ብፁአን አባቶቻችን በውጭው አለም ቤተ - ክርስቲናችን አብባለች(ተስፋፍታለች)፡፡ እስቲ ወደ ብፁእነታቸው ልመለስ





እንዲያው እንደ እኔ ውጫዊ ገፃቸውን ተክለ አቋማቸውን አስተውሎ እንዲሁ ላየ ሰው ብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ ልክ ያለፉትን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሀይማኖትን ነው የሚመስሉት ይገርማል ብፁዕነታቸው ለተሰበሰበው ምዕመን ቃለምዕዳንና ቡራኬ የሰጡ ሲሆን በበህላችን በስርአታችን እንድንኮራ ሐይማኖታችንን እንድንጠብቅ በእግዚአብሄር ቤት ዘወትር ሳንጠፋ እንድናመልክ ከእውነት የሆነ የውስጣዊ ስሜታቸውን በግልፅ አበክረው መክረው የእለቱን ቃለ ምዕዳን ከሰጡን በኋላ ፕሮግራሙን በፀሎት አሳርገውልናል፡፡

እያሱ የምድርን ሁሉ ጌታ የእግዚአብሄርን ... *የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናት በህዝቡ ፊት ታጅበው ይሄዱ ነበር ኢያሱ 3:14* እኛም የአዲስ ኪዳን



ህይወታችን ዙፋን በስርአት ለማድመቅ እሁድ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን አስተርእዮ እና የመላኩ የቅዱስ ኡራኤልን በአል በደመቀ ሁኔታ አክብረን ውለናል የእየሱስ ክርስቶስ ሕቡዕ ስሙ የተፃፈበት የቅዱሳኑ መታሰቢያ



የቃልኪዳኑን ታቦታት ለማንገስ ሕዝቡ በእመቤታችንና በኡራኤል ስም ሊባረክ ከቅዱሳንም ምልጃንና በረከትን እንዲያገኝ ከቅዳሴው ሰዓት ጀምሮ ተሰብስቧል:: በቤተክርስቲያናችን ስርአት መሰረት በእለቱ ሁለት የቤተክርስቲያን አገልጋዮች የቅስና መአረግ ከብፁዕነታቸው በእግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ ፈቅዶላቸው ተቀብተዋል::





አያስቀናም በዚህችው ቤተክርስቲያናችን እኮ ባለፈው በአረጋዊው በብፁዕ አባታችን በአቡነ ኤልያስ የምንኩስና ስርአትም ተከናውኗል ለአንድ ወንድማችንም የዲቁና መዐረግ መስጠታቸው ይታወሳል አሁን ደግሞ የመነኮሱት አባ  መጋቢ ጌታነህና መምህር ዲያቆን ገብረ ማርያም በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የቅስና ማዕረግ ተሰጣቸው መታደል እኮ ነው በሰው ሐገር እግዚአብሄር ልጆቹን ሲያከብር ይህም እኮ እራሱን የቻለ ትልቅ በዓላችን እና ደስታችን ነው።

ከቅዳሴው በኋላ ታቦታቱን አባ ሀብተ እየሱስና ቀሲስ አለምሰገድ አክብረዋቸው በደብሩ አገልጋዮች መዘምራንና ምዕመናን በሆታና በእልልታ ታጅበው ወጥተዋል አቤት ሲያስደስት እንዲህ ያለም የለም

ህዝቡ ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ እንዲሉ ሆኗል ሴቱ በአገር በአል ልብስ አሸብርቋል ወንዱም በአሉን አድምቋል መቸም በጥሩ በአላችንና ስርአታችን ወልደ ዋህድ እየሱስ ክርስቶስን የምታመልክ ቤተክርስቲያናችን ታኮራናለች ከንግሱም ላይ ለእመቤታችንና ለኡራኤል መንበር በጥሩ ሁኔታ ለማሰራት ብፁእ አባታችን አቡነ መቃርዮስ ምዕመናንን እጃችሁን ዘርጉ በማለታቸው በእለቱ ከ55 ሽህ ራንድ በላይ ሁሉም በፍቅርና በቅንነት እጁን ዘርግቷል። የእለቱ በአል መቸም እፁብ ድንቅ ሆኖ ነበር ተከበሮ ውሎ ታቦታቱን አጅበን ወጥተን ካነገስን በኋላ በሆታና በእልልታ እግዚአብሄርን እያመሰገንን ወደ መንበራቸው  የመለስነው።

ዮሀንስ *ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ ገዳይ ነው ነፍሰ ገደይ የሆነ ሁሉ የእግዚአብሄር መንግስት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ 1ኛ ዮሀ.3:15* እንዳለን እንኳንም ልክ እንደ ገና ሰሞኑ የፈተና ሰሞን እርስ በእርስ በተንኮል በጥላቻ በቅንአትም መንፈስ ተወጥነን የግላዊ አመለከከት ልዩነታችን ወደ ክፋት ተቀይሮ ጥቂቶቻችን በጆርባችን በውስጠ አዋቂ ለየዝነው ኢ - ክርስቲያናዊ አላማ የቤተ-ክርስቲያናችንና የሐይማኖታችን ስም በክንቱ አላስነሳን። ለዚህ እኮ ነው ብርሐነ አለም ጳውሎስ ***በሮሜ መልዕክት 2 - 24 ላይ በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአህዛብ መካከል የሰደባል ያለው።***



*መቼም ሰሞኑን አባቶቻችንና እንግዶቻችን ተገኝተው በሰጡት አገልግሎት በተሰጠው ትምህርተ ወንጌል ህይወታችን ለመለወጥና ክፉውን ስራ ለይተን የእግዝአብሔር መንፈስ ቅዱስን ስራ ለመፈጸም ካልተጋን ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው* ***እግዝአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዝአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው ሮሜ 1 - 28*** *ያለው የቃሉ ተፈፃሚዎች ሆነን እንገኛለን።*



ወደ ማጠቃለያ ጉዳዩ ልግባና ብፁእ አቡነ መቃርዬስና ዶክተር ዲያቆን ናትናኤል ስለእኛ ስለስደተኞች ጉዳይ በሳውዝ አፍሪካ ጉዳዩ በሚመለከታቸው በተለያዩ ቢሮዎች የውጪ እርዳታ ድርጅቶች ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ያለእረፍት በእኛ በወገኖቻቸው ጉዳይ የተወያዩልንና የተነጋገሩልን ሲሆን ከዚህም መካከል :-

1. በተለያየ እስር ቤት የሚገኙትን ወገኖቻችን ጎብኝተዋል። በመኖሪያ ፈቃድ (Home Affairs) ችግር የታሰሩትን ስደተኞች ለማስፈታት ከቀይ መስቀል ፤ ከሕዩማን ራይት እና ከህግ ባልሙያዎች ጋር ተነጋግረዋል።

2. ለስደተኞች ጉዳይ በይናይትድ ኔሽን (UNHCR) ጋርና ከውጭ ኤምባሲዎች ጋር በresettlement ጉዳይ ለመነጋገር ቀጠሮ ይዘዋል።

3. በዜኖ ፎቢያ ምክንያት ንብረታቸውን ያጡና የተለያየ ችግር ደርሶባቸው በከምፕ ውሰጥ የሚገኙትን ወገኖቻችን ጎብኝተው ያነጋገሩ ሲሆን በዊኒፒንግ ቅድስት ማርያም የስደተኛዋ ቤተ/ክርስቲያናችን ካናዳ በአባ ፍቅረ ሥላሴ አማካይነት ለመውሰድ በተደረገላቸው ፕሮሰስ የካናዳን ኤምባሲ በማነጋገር ቀጠሮ አስይዘዋል።



*የሰበካ ጉባኤ ኮሚቴዎች ከአባቶች ጋር*

እንዲህ ነው አባትነትና ወንድምነት የወገን ፍቅር:: ብፁእነታቸው እና ዶክተር ናትናኤል ሰሞኑን በኛ በክፋት ቤተ - ክርስቲያናችንን ለማናወጥ እኛን ለማለያየት ክፍተት አይቶ ለተነሳው መንፈስ በህጋዊ ሁኔታ ቤተ - ክርስቲያናችን ለሰደተኛው ለማረጋገጥ ህጋዊ እውቅናን አሰጥተውናል:: የኢትዮጵያዊነት አባትነት የወገን ግዴታችውን ተወጥተዋል:: እንዲህ ነው እንጂ ከላይኛው አባት የተሰጠን ፀጋ ለወገንና ለህዝብ በመጠቀም ሐላፊነትን በአግባብ በመወጣት ለህሊና ዘላለማዊ ሠላምና እረፍት መስጠት:: ክቡር አባታችንና መምህራችን አባ ወልዴም በመፅሀፍ ***የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው ኤፌሶን 6:17*** እንዳለ ይህንን የእግዚአብሔር ቃል ይዘው በሌላ ጉዳያችሁ አትምጡብኝ ያሉ ይመስላል ከላይ በተሰጣቸው ወንጌልን ያለድካም ይሉታል አቤት መታደል ሁላቸውም በተሰጠቸው ኃላፊነት ***ጌታ እራሱን አሳልፎ እስኪሰጥ ድርስ ያለዋጋ እንዲሁ በባዶ እንደወደደን 3 16 5 6*** ህያው ቃሉን ወደ ህይወታቸው ቀይረው መንጋቸውንና ወገኖቻቸውን ሊያገለግሉ ከያሉበት ዋጋ ሊከፍሉልን የተገኙልን መታደላችን !!! በዚህ ጥሩ ሠላምና ነፃነት እንኳን አምብዛም ሳይኖራት በስደት በምንኖርባት ሀገር እግዚአብሔር አብዝቶ ባረከን::

*እግዚአብሔር ለህዝቡ ሀይልን ይሰጣል ፤እግዚአብሔር ህዝብን በሠላም ይባርካል መዝ 28 - 11*

ይህን ሁሉ የሰጠን እግዚአብሔር ይባረክ::

## ወስብሐት ለእግዚአብሐር